# ከኮፐንሃገን መልስ

*ክንፉ አሰፋ፣ ከአምስተርዳም*

*የአፍሪካው "ተደራዳሪ" ከኮፐንሃገን መልስ እንደወትሮው በቴሌቭዢን ብቅ አሉ። የአፍሪካን ተደራዳሪ ቡድን በመምራትም ድል ተቀዳጅተው መመለሳቸውን አወሱ፡ እሳቸው ያቀረቡት ሃሳብም በበለጸጉ ሃገሮች ተቀባይነትን እንዳገኘ አበሰሩ። የኮፐንሃገኑ ድርድር የአፍሪካን ጥቅም የሚያስጠብቅ ስምምነት ላይ መድረሱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲያበስሩ አይናቸውን አልጨፈኑም። ራሳቸውንም አላከኩም። በውስጣቸውም አንዳች የጥፋተኝነት መንፈስም አይታይባቸወም።*

*ታሪክ እንደ ሰሩት ቀደምቱ የአፍሪካ መሪዎች፤ እንደነ ጆሞ ኬንያታ፣ እንደነ ሁፍዌት ቩዋኜ፣ እነደነ ክዋሜ ንክሩማ፣ እንደ ቀዳማዊ ኃይለ ሰላሴ... ለአህጉሪቷ ጥቅም ትልቅ መስዋእት መክፈላቸውን አቶ መለስ ሲያበስሩ የሄጉን የኢትዮ-ኤረትራ ድንበር ውሳኔ ድራማ ያስታውሰናል። የፍርዱን ሂደት ተከታትለው ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት አቶ ስዩም መስፍን በድንበሩ ያሉ አከራካሪ መሬቶች ሁሉ ለኢትዮጵያ መሰጠታቸውን ቴሌቪዥን ላይ ብቅ ብለው በድፍረት ተናገሩ። ሕዝቡም በነጋታው ደስታውን ባደባባይ እንዲገልጽ ተገደደ።...እነ አቶ ስዩም በሃሰተኛ ወሬ ሕዝቡን ቀልደውበት ሲያብቁ፡ በውስጣቸው አንዳችም የጥፋተኝነት ስሜት አይታይባቸውም ነበር።*

*ከኮፐንሃገን መልስ በሰጡት 'ጋዜጣዊ መግለጫ' የጥፋተኝነቱ ስሜት አይኑራቸው እንጂ፡ የነበረው 'ሙድ' አቶ መለስ ሲሸኙ ከነበረው 'ሙድ' ግን የተለየ ነው። የአፍሪካው "ተደራዳሪ" ከኢትዮጵያ ሲነሱ የነበረው ቤተ-መንግስታዊ ግብዣ አምባሳድሮችን ሳይቀር ያስገርመ፤ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው እንደነበር ይነገራል። ይህንን የመልካም ምኞት ምሽት ያዘጋጁት እና ዝግጅቱን ሲመሩ የነሩት እነ አትሌት ሃይሌ ገ/ስላሴ፡ አርቲስት ሰራዊት ፍቅሬ፡ ጌትነት እንየው፤... አርቲስቶች፡ አትሌቶች፡ ምሁራን፡ አርሶ አደሮች፡ ወዘተ. እውነተኛውን የኮፐንሃገን ድርድር ውጤት ሲሰሙ ምን ይሉ ይሆን?*

*ከመቼወም በላይ እጅግ አወዛጋቢ የነበረው የዘንድሮው የኮፐንሃገን ድርድር እንዳበቃ በታላቋ ብሪታንያ ግሪን ፒስ በመባል የሚታወቀው የአካባቢ ጥበቃ ዳይሬክተር፡ ጆን ሳውቨን እንዲህ ነበር ያሉት፡* "The city of Copenhagen is a crime scene tonight, with the guilty men and women fleeing to the airport." *በጥሬው ሲተረጎም፡ "በዛሬዋ ምሽት የኮፐንሃገን ከተማ የወንጀል መድረክ ሆናለች።ጉባኤውን ጨርሰው ወደ አውሮፕላን ጣቢያው የሚበሩት ወንዶችና ሴቶች በጥፋተኝነት መነፈስ ይታይባቸዋል፡" እንደማለት ነው። ሚ/ር ጆን ይህንን ሲሉ ያደጉ ሀገሮች በተለይ በአፍሪካ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችለውን ስምምነት መጫናቸውን ለመኮነን ነበር።*




*ከሁለት አመታት ያላነሰ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የአየር ብክለት ተሟጋቾችና ኤክስፐርቶች ሲደክሙበት የነበረው ከኮፐንሃገኑ የአየር ንብረት ለውጥ*

ድርድር ውጤት በአጭሩ እንዲኮላሽ ተደረጓል። አቶ መለስ ከኒኮላስ ሳርኮዚ የተሰጣቸው፡ “የዓለም ሙቀት መጠን ከ2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በላይ እንዳይጨምርና 10 ቢሊዮን ዶላር ካሳ ክፍያ” የሚለውን ሰነድ የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲው ኢኮኖሚስትና የቡድን 77ቱ ተደራዳሪ የሆኑት ሚ/ር ሉሙምባ ዲ አፒንግ ሲገልጹት፤

“ይኸ ለአፍሪካ እጅግ አደገኛ ነው። በሳይንስ 2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ማለት ለአፍሪካ 3.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ማለት ነው። የተጠቀሰዉ 10 ቢሊዮን ዶላር ደግሞ በአደጋው ለሚያልቁት አፍሪካውያን የመቃብር ሳጥን መግዣ እንኳን የሚበቃ አይደለም።” ብለው ነበር።

ዓለማችንን እያሳሰበ ያለው የካርቦን ልቀትና እጅግ እየጨመረ የመጣው የሙቀት መጠን በተለይ ላለፉት ሁለት አመታት በስፋትና በጥልቀት ሲነገርለት ሰንብቷል። የአለም ዓይን ሁሉ ለመፈትሄው በኮፐንሃገን ላይ አርፏል። የአለማችንን የአካባቢ ብክለት ችግር ሊቀንስ ይችላል የተባለለት የ1997ቱ የኪዮቶው የአየር ለዉጥ ስምምነት በአሜሪካ እንቢተኝነት ሳቢያ ተግባራዊ ሳይሆን ቢቆይም፡ የባራክ ኦባማ አስተዳደር መምጣት የአሜሪካን አቋም በመቀየር የፖሊሲ ለውጥ ያደርጋል የሚል ተስፋ አጫሪ እምነት ጥሎ ነበር። የአካባቢ ጥበቃ ተሟጋቾች በዚህ ላይ ያለ እረፍት በመስራት፤ የአለምን ሕዝብ ከኋላቸው በማሰለፍና የድርድር የባላይነት ስሜት በመያዝ ተስፋ ሰንቀው ነበር ወደ ኮፐን ሃገን ያመሩት።




የምድራችን የሙቀት መጠን መጨመር በእጅጉ እየጎዳት ያለችው አፍሪካም የሞራል የበላይነት ይዛ ነበር ለኮፐንሃገኑ የአየር ንብረት ጉባኤ ስትዘጋጅ የነበረው።

“እኛ ያልፈለግነው ወይንም ከኛ ፈቃድ ውጭ የሆነ አንዳች ስምምነት ቢኖር አባሎቻችንን በመጠቀም ህገ-ወጥ እናደርገዋለን። አህጉራችንን አስገድዶ የሚደፍር አይነት የስምምነት ሃሳብ ቢኖር ጉባኤውን ረግጠን እንወጣለን.. ለ አየር ንብረቱ መዛባት ካሳ እንዲሆን 40 ቢሊዮን ዶላር እንጠይቃለን።” ነበር ያሉት በጉባኤው ላይ የአፍሪካን ተደራዳሪ ቡድን እመራለሁ የሚሉት አቶ መለስ ዜናዊ።

ሳምንቱን ሙሉ የኮፐንሃገን ቤላ ማዕከል በከፍተኛ ውጥረት ላይ ሰንብቷል። ከውስጥ በተደራዳሪዎች፤ በአካባቢ ጥበቃ ተሟጋቾችና በሃያላን መንግስታት እየተደረገ ያለው የጋለ ውይይት ውጥረቱን ከምን ጊዜውም በላይ አጠንክሮታል። በውጭ ደግሞ በ10ሺዎች የሚቆጠሩ የድሃ ሃገር ተሟጋቾች በረዶ ሳይበግራቸው ያለማቋረጥ ይጮሃሉ። በሳምንቱ ማብቂያም በአውሮፓ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወ/ት ብረቱካንን ጨምሮ በርካታ የህሊና እስረኞችን ፎቶ በመያዝ በ አቶ መለስ ላይ የተነሳውን ተቃውሞ አጉልተውት ነበር።

ምእራባውያን እንደዋዛ ችላ ብለውት የነበረው ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ ከአለም ዙሪያ 45,000 የአካባቢ ጥበቃ ተሟጋቾች ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል። ከ 30-40 ሺህ የሚሆኑ ደግሞ የበለጸጉ ሃገሮች የአየር ብክለት ችግር ላይ ተቃውሞ ለማሰማት የመጡ ናቸው። የቤላ ማእከል ተጨናነቀች።

የተቃውሞው ስሜት እየጋለ ሲመጣ ለዴንማርክ ፖሊሶች አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጠረባቸው። እናም የሀገሪቱ ፓርላማ በአስቸኳይ በመሰብሰብ ለፖሊስ የ'ማሰር ስልጣን' የሚሰጥ ህግ ማውጣቱን የሃገሪቱ መገናኛ ብዙሃን ዘገቡ። በመቶዎች የሚቆጠሩ ተቃዋሚዎችም እየተያዙ እንዲታሰሩ ተደረገ። ተቃውሞው ግን ሊቆም አልቻለም።

"One Africa, one degree" - "Two degrees is suicide" "አንድ አፍሪካ - አንድ ዲግሪ! ሁለት ዲግሪ ራስን በራስ ማጥፋት ነው!" የሚለው ጩኸት ጎልቶ ይሰማል፡ ከአፍሪካውያንና የአፍሪካ ወዳጆች። በቀዝቃዛው በረዶ ላይ ለቀናት እየጮሁ ያሉት ወገኖች ከድርድሩ አንዳች በጎ ነገር እየጠበቁ ናቸው። የአፍሪካው "ተደራዳሪ" ለምእራባውያን ሃገሮች የሰጡት የማስፈራርያ ቃል አንዱ ተስፋቸው ነበር። ከዛ ውጭ ደግሞ ከአፍሪካ ጀርባ የአለም ድጋፍ አለ። የበለጸጉ ሃገሮች የሚለቁት የካርበን ልቀት እና ሰው ሰራሹ የሙቀት መጠን መጨመር ከሁሉም በላይ አህጉረ አፍሪካን እያጠቃ መሆኑን በየሎቢው ግልጽ በሆነ መንገድ ይናገራሉ። ለዚህም ከገንዘቡ ይልቅ ያሳሰባቸው የሙቀት መጠኑ መጨመር ጉዳይ ነው።

የቤላ ማእከል በዚህ አይነት የውስጥ እና የውጭ ውጥረት ውስጥ ባለበት ሰዓት የፈረንሳዩ ሳርኮዚ እና "የኛው" ሰው ፓሪስ ከሚገኘው ኤሊሴ ቤተ-መንግስት በቴሌቭዥን መስኮት ብቅ አሉ። ጋዜጠኞችንም ሰብስበው "ስምምነት ላይ ደርሰናል! 2 ዲግሪና 10 ቢልየን ዶላር!" ሲሉ ሰበር ዜናውን ለአለም ህዝብ አረዱ።

ብዙዎች የሚያዩትንና የሚሰሙትን ለማመን ተቸገሩ። ነገሩ እውነት መሆኑን ያረጋገጡት "አንድ አፍሪካ አንድ ዲግሪ!" እያሉ ሲጮሁ የነበሩት ሰልፈኞች፣ ወክለነዋል ያሉት ሰው ሁለተኛ አፍሪካ ከ2 ዲግሪ ጋር ሆኖ ብቅ ሲልባቸው መፈክሮቻቸውን ለመድገም ተቸገሩ። ከአፍሪካ ልኡክ ጋር ወደ ስፍራው የተጓዙት እነ ሮበርት ሙጋቤና እነ አብዱላሂ ዋዴም ግራ ተጋቡ።

መለስ የፓሪስና የለንደን ውሎአቸውን ጨርሰው ወደ ኮፐንሃገን ቤላ አዳራሽ ሲገቡ ባይተዋር እንደነበሩ መገናኛ ብዙሃኑ ዘግበዋል። አሁን ግልጽ የሆነ ልዩነት ተፈጠረ። አንድ አፍሪካዊ ተደራዳሪን በመጥቀስ አይ.ፒ.አይ. ሲዘግብ፡ "We have been asked to sign a suicide pact... It is unfortunate that after 500 years-plus of interaction with the West፣ we [Africans] are still considered 'disposables'... " ወደ አማርኛው ሲመለስ “ራስን በራስ የመግደል ዉል ላይ እንድንፈርም ተጠየቅን... አለመታድል ሆኖ ከ500 አመታት በላይ ከምእራቡ አለም ጋር ግንኙነት አድርገናል ብንልም፡ እኛ አፍሪካውያን አሁንም እንደ አላቂ እቃ ነው የተቆጠርነው።” ብሏል።

ማንቶ ፋካቲ የተባለው ሌላው ጸሃፊ ደግሞ “Zenawi stands alone in Copenhagen” “በኮፐንሃገን መለስ ብቻውን ቀረ!” ሲል ያደጉ ሃገሮችን ጥቅም የሚያስጠብቀው የሳርኮዚ - መለስ ስምምነት በአፍሪካውያን ተቀባይነት እንዳላገኘና ይልቁንም አንዳንዶች የአቶ መለስ ዜናዊ አፍሪካን የመወከል ስልጣን እንዲነሳ መጠየቃቸውን ዘግቧል።

የመለስ መግለጫ እንደተሰማ ለአፍታ ግርታን ፈጠረ። የተቃውሞው አቅጣጫም ተቀየር። የበለጸጉ ሃገሮችን ሊያወግዙ የመጡት የፓን-አፍሪካ ንቅናቄ መሪዎችና የአለም አካባቢ ጥበቃ ተቋማት ውግዘቱን ወደ አቶ መለስ አዞሩት። "አቶ መለስ ስለ አፍሪካ ሊያወሩ አይችሉም" ሲሉ የአፍሪካ ፓርላማ አባላትና የሲቪክ ማህበር መሪዎች ወዲያው መግላጫ አወጡ።

"የ አይ.ፒ.ሲ.ሲ. ሳይንስ ግልጽ ነው። 2 ዲግሪ ማለት ለአፍሪካ 3.6 ዲግሪ ነው። ይህ ደግሞ ለአህጉሪቱ የሞት ፍርድ ማለት ነው።" ይላሉ የፓን አፍሪካ ፓርላማ ኔትወርክ ፕሬዚዳንት አዉዱ እምባያ። የፓን አፍሪካ አየር ጸባይ ጥምረት መሪ የሆኑት፡ ሚ/ር ሚቲካ ምዌንዳ ሲናገሩ፡ "አቶ መለስ ለርካሽ ጥቅም ሲሉ የአፍሪካን ሕዝብ ህይወትና የአፍሪካን ተስፋ መሸጥ ከፈለጉ ያንን ያድርጉ፣ ነገር ግን ይህ የአፍሪካ አቋም አይደለም።" ሲሉ አውግስቲን ጃምንሺ የተባሉት የጥምሩ

ወኪል ደግሞ "እያንዳንዱ አፍሪካዊ ይዞት የተነሳውና የሚታገልለት መርህ አለ፡ ይህም ሳይንስን የተመረኮዘ 45% ቅናሽ እና 400 ቢሊዮን ዶላር ካሳ ነው።" ሲሉ ተደምጠዋል።

ኤን.ቲ.ቪ. በመባል የሚታወቀው የኬንያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ ከስፍራው ስትዘግብ፡ "የአቶ መለስ ስምምነት መላውን አፍሪካዊ ያሳዘነ ነው። ስምምነቱ በአፍሪካ አህጉር ሰቆቃን የሚያስከትል ሲሆን በአንጻሩ ለአደጉ ሀገሮች ፋታን ሰጥቷቸዋል።" ብላለች። በአካባቢ ጥበቃ ተሸላሚ የሆነችው የእንግሊዝዋ ጋዜጠኛ ናኦሚ ክሌይንም ዘ ጋረዲያን በተባለው በታዋቂው የእንግሊዝ ጋዜጣ ላይ፡ "በዘጠነኛው ቀን አፍሪካ መስዋእት ሆነች" በሚል ርእስ ባሰፈረችው ዘገባ፡ ሳርኮዚ እና መለስ የተስማሙበት ሰነድ ከ 300 — 600 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎችን ለከፋ አደጋ የሚጥል መሆኑን በመጥቀስ፡ "አቶ መለስ ዜናዊ ቀድሞ የነበራቸውን አቋም በመቀየር ለዚህ ስምምነት መድረሳቸው ለውለታው ምን እንደተቀበሉ እስካሁን አላወቅንም።" ብላለች።

በእርግጥም እንደ ናኦሚ ላሉት ለአፍሪካ ቀና አሳቢዎች ጉዳዩ እንቆቅልሽ ሊሆን ይችላል። በአቶ መለስ ታስቦና ተጠንቶ የተሰራው ድራማ፡ ለብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ እምብዛም አያስደንቅም። በአጭሩ አቶ መለስ አንገብጋቢውን የአህጉራችንን ጉዳይ ለምእራባውያን አሳልፈው በመሰጠትና ለምዕራባውያኑ የሚጠቅም ስምምነት ላይ በመድርስ፤ የአፍሪካን ችግር የኢህአዴግ ግዚያዊ የፖለቲካ መነገጃ አድርገውታል።

ይህ ደግሞ ያልታሰበበት ጉዳይ አይደለም። መለስ በኮፐንሃገኑ የአየር ንብረት ጉባኤ ላይ የአፍሪካን ተደራዳሪ ቡድን መርተው ለመሄድ አዲስ አባባ ያሉ የአፍሪካ ዲፕሎማቶች ላይ ከፍተኛ ወጪ በማድረግ እንዳግባቡ የሚጠቁሙ መረጃዎች ብቅ እያሉ ነው። ሎቢ በማድረግና የወቅቱ የኔፓድ ሊ/መንበርነታቸውን ስልጣን በመጠቀም መለስ ብዙ ከጣሩ በሁዋላ ቦታውን ማግኘት ቻሉ። እስከመጨረሻዋ ሰአትም ምእራባውያኑን የማስፈራራት ስልት ተጠቀሙ። አቶ መለስ ይህንን ሁሉ ድካም ሲያደርጉ የነበረው ካላንዳች ምክንያት አልነበርም። መለስ በሃገር ውስጥ የሰብአዊ መብት ጥሰታቸው ሳቢያ በምእራባውያኑ አለም በክፉ አይን እንደሚታዩና በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ መንግስታቸው ጥቁር ነጥብ የተጣለበት መሆኑን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ፡ ፊታቸውን ያዞሩባቸውን ሃያላን መንግስታት ሊክሱ የሚችሉበት አይነተኛ መንገድ ይህ ብቻ በመሆኑ ነው።

ቀድሞ ይጫወቱበት የነበረው የሶማሊያ ካርታ በመበላቱ፡ በተለይ ከኦባማ አስተዳደር ጋር ሊያቀራርባቸው የሚችል ሌላ መንገድ አልነበርም። ከፊት ፊጥጦ የሚጠብቃቸው የምረጫ ፈተና ከመድረሱ በፊት አፍ ማስያዣ፡ እጅ መንሻ ሆኖ የቀረበ አጀንዳ ነው የሆነላቸው የኮፐንሃገኑ ስምምነት። ስለሆነም ለግል የፖለቲካ ትርፍ ሲሉ አፍሪካ ላይ የሚፈርደውን ስምምነት ሳያንገራግሩ ተቀበሉት።

በአፍሪካን ሳይሆን በበለጸጉ ሃገሮች አቋም ላይ በመስማማት የነ ባራክ ሁሴን ኦባማን ቡራኬ ካገኙ በሁዋላ መለስ ድራማውን በ "ድል" ደመደሙት።

ኢትዮጵያውያን ሊያነግበግበን የሚገባው የአቶ መለስ በአፍሪካ ጥቅም ላይ ተደራድሮ የግል ፖለቲካ ትርፍ ማካበቱ አይደለም። ከዚያ ይልቅ "ኢትዮጵያ የአፍሪካን ጥቅም ለበለጸጉ ሃገሮች አሳልፋ ሰጠች" እየተባለ በየመገናኛ ብዙሃኑ የምናየው፡ የአቶ መለስ አቋም እንደ ኢትዮጵያ አቋም ተደርጎ መወሰዱ ነው።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ የነጻነት ተምሳሌት ብቻ ሳትሆን በጸረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል ፊር ቀዳጅነት፡ በፓን-አፍሪካን ንቅናቄና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ ባለውለታም መሆንዋን ታሪክና ትውልድ የሚመሰክሩላት ናት።

ዛሬ አቶ መለስ በክፉ አስጠሯት።